# ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ።

(ክለሳ.1.20020507)

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ።

ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ በዳርዮስ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ በስምንተኛው ፡ ወር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደአዶ ፡ ልጅ ፡ ወደበራክዩ ፡ ልጅ ፡
ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ዘካርያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

2 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአባቶቻችኹ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ተቈጥቶ ፡ ነበር ።

3 ፤ ስለዚህ ፥ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፥ ይላል ፡
የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ እኔም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እመለሳለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

4 ፤ የቀደሙት ፡ ነቢያት ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ሰብከዋል ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፦ ከክፉ ፡ መንገዳችኹና ፡ ከክፉ ፡ ሥራችኹ ፡ ተመለሱ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ አልሰሙም ፥ እኔንም ፡
አላደመጡም ፤ እንደ ፡ እነርሱ ፡ አትኹኑ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

5 ፤ አባቶቻችኹ ፡ ወዴት ፡ ናቸው ፧ ነቢያትስ ፡ ለዘለዓለም ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉን ፧

6 ፤ ለባሪያዎቼስ ፡ ለነቢያት ፡ ያዘዝኋቸው ፡ ቃሎቼና ፡ ሥርዐቴ ፡ በአባቶቻችኹ ፡ ላይ ፡ አልደረሱምን ፧ እነርሱም ፡
ተመልሰው ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመንገዳችንና ፡ በሥራችን ፡ መጠን ፡ ያደርግብን ፡ ዘንድ ፡ እንዳሰበ ፡
እንዲሁ ፡ አድርጎብናል ፡ አሉ ።

7 ፤ በዳርዮስ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ ሳባጥ ፡ በሚባል ፡ በዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ወር ፡ በኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡
የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደአዶ ፡ ልጅ ፡ ወደበራክዩ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ዘካርያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

8 ፤ እንሆም ፥ አንድ ፡ ሰው ፡ በመጋላ ፡ ፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ በሌሊት ፡ አየኹ ፥ ርሱም ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ባሉ ፡
በባርሰነት ፡ ዛፎች ፡ መካከል ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ በስተኋላውም ፡ መጋላና ፡ ሐመር ፡ ዐምባላይም ፡ ፈረሶች ፡ ነበሩ ።

9 ፤ እኔም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧ አልኹ ። ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡
መልአክ ፦ እነዚህ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ አሳይኻለኹ ፡ አለኝ ።

10 ፤ በባርሰነት ፡ ዛፎች ፡ መካከልም ፡ ቆሞ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፦ እነዚህ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይመላለሱ ፡ ዘንድ ፡
እግዚአብሔር ፡ የላካቸው ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

11 ፤ በባርሰነት ፡ ዛፎች ፡ መካከልም ፡ ቆሞ ፡ የነበረውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፦ በምድር ፡ ላይ ፡
ተመላለስን ፥ እንሆም ፥ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ ዐርፋ ፡ ተቀምጣለች ፡ ብለው ፡ መለሱለት ።

12 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ መልሶ ፦ አቤቱ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ የተቈጣኻቸውን ፡
ኢየሩሳሌምንና ፡ የይሁዳን ፡ ከተማዎች ፡ የማትምራቸው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧ አለ ።

13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መልሶ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ ለነበረው ፡ መልአክ ፡ በመልካምና ፡ በሚያጽናና ፡ ቃል ፡
ተናገረው ።

14 ፤ ስለዚህም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ስበክ ፡ እንዲህም ፡ በል ፦ የሰራዊት ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ በታላቅ ፡ ቅንአት ፡ በኢየሩሳሌምና ፡ በጽዮን ፡ ቀንቻለኹ ።

15 ፤ እኔ ፡ ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ተቈጥቼ ፡ ሳለኹ ፡ እነርሱ ፡ ክፋትን ፡ ስላገዙት ፥ ባልተቸገሩት ፡ አሕዛብ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡
ተቈጥቻለኹ ።

16 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በምሕረት ፡ ተመልሻለኹ ፤ ቤቴ ፡
ይሠራባታል ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ላይ ፡ ገመድ ፡ ይዘረጋበታል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።



www.ethiopianorthodox.org

17 ፤ ደግሞም ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ስበክ ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከተማዎቼ ፡ ደግሞ ፡
በበጎ ፡ ነገር ፡ ይረካሉ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ ጽዮንን ፡ ያጽናናል ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡ ደግሞ ፡ ይመርጣል ።

18 ፤ ዐይኖቼንም ፡ አንሥቼ ፥ እንሆ ፥ አራት ፡ ቀንዶች ፡ አየኹ ።

19 ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረውን ፡ መልአክ ፦ እነዚህ ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧ አልኹት ። ርሱም ፦ እነዚህ ፡
ይሁዳንና ፡ እስራኤልን ፡ ኢየሩሳሌምንም ፡ የበተኑ ፡ ቀንዶች ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ።

20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አራት ፡ ጠራቢዎች ፡ አሳየኝ ።

21 ፤ እኔም ፦ እነዚህ ፡ የመጡት ፡ ምን ፡ ሊሠሩ ፡ ነው ፧ አልኹ ። ርሱም ፦ አንድ ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ እስከማያነሣ ፡
ድረስ ፡ እነዚህ ፡ ቀንዶች ፡ ይሁዳን ፡ የበተኑ ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ ግን ፡ ሊያስፈራሯቸው ፥ የይሁዳንም ፡ አገር ፡ ይበትኑ ፡
ዘንድ ፡ ቀንዳቸውን ፡ ያነሡትን ፡ የአሕዛብን ፡ ቀንዶች ፡ ሊጥሉ ፡ መጥተዋል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

## ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ ዐይኖቼንም ፡ አነሣኹ ፤ እንሆም ፥ በእጁ ፡ የመለኪያ ፡ ገመድ ፡ የያዘ ፡ አንድ ፡ ሰውን ፡ አየኹ ።

2 ፤ እኔም ፦ አንተ ፡ ወዴት ፡ ትኼዳለኽ ፧ አልኹ ። ርሱም ፦ የኢየሩሳሌምን ፡ ወርድና ፡ ርዝመት ፡ ስንት ፡ መኾኑን ፡
ሰፍሬ ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ እኼዳለኹ ፡ አለኝ ።

3 ፤ እንሆም ፥ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡ መልአክ ፡ ወጣ ፥ ሌላም ፡ መልአክ ፡ ሊገናኘው ፡ ወጣ ፥

4 ፤ እንዲህም ፡ አለው ፦ ሩጥ ፥ ይህንም ፡ ጕልማሳ ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ ኢየሩሳሌም ፡ በውስጧ ፡ ካሉት ፡ ሰዎችና ፡
እንስሳዎች ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ቅጥር ፡ እንደሌላቸው ፡ መንደሮች ፡ ኾና ፡ ትኖራለች ።

5 ፤ እኔ ፡ በዙሪያዋ ፡ የእሳት ፡ ቅጥር ፡ እኾንላታለኹ ፥ በውስጧም ፡ ክብርን ፡ እኾናለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

6 ፤ እናንተ ፡ ሆይ ፥ ከሰሜን ፡ ምድር ፡ ሽሹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እንደ ፡ አራቱ ፡ የሰማይ ፡ ነፍሳት ፡
በትኛችኋለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

7 ፤ አንቺ ፡ ከባቢሎን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ጋራ ፡ የምትኖሪ ፡ ጽዮን ፡ ሆይ ፥ ኰብልዪ ።

8 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ከክብሩ ፡ በኋላ ፡ ወደበዘበዟችኹ ፡ አሕዛብ ፡
ልኮኛል ፤ የሚነካችኹ ፡ የዐይኑን ፡ ብሌን ፡ የሚነካ ፡ ነውና ።

9 ፤ እንሆ ፥ እጄን ፡ በላያቸው ፡ አወዛውዛለኹ ፥ ተገዝተው ፡ ለነበሩት ፡ ብዝበዛ ፡ ይኾናሉ ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡
እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ ታውቃላችኹ ።

10 ፤ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ መጥቼ ፡ በመካከልሽ ፡ እኖራለኹና ፡ ዘምሪ ፥ ደስም ፡ ይበልሽ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ።

11 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጠጋሉ ፥ ሕዝብም ፡ ይኾኑኛል ፤ በመካከልሽም ፡
እኖራለኹ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ ታውቂያለሽ ።

12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይሁዳን ፡ ዕድል ፡ ፈንታው ፡ አድርጎ ፡ በተቀደሰችው ፡ ምድር ፡ ይወርሰዋል ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡
ዳግመኛ ፡ ይመርጣል ።

13 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከተቀደሰ ፡ ማደሪያው ፡ ነቅቷልና ፥ ሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ሆይ ፥ በፊቱ ፡ ዝም ፡ በል ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

## ምዕራፍ ፡ 3 ።

1 ፤ ርሱም ፡ ታላቁን ፡ ካህን ፡ ኢያሱን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ አሳየኝ ፥ ሰይጣንም ፡ ይከሰው ፡ ዘንድ ፡
በስተቀኙ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ ሰይጣን ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ይገሥጽኽ ፤ ኢየሩሳሌምን ፡ የመረጠ ፡



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ፡ ይገሥጽኽ ፤ በእውኑ ፡ ይህ ፡ ከእሳት ፡ የተነጠቀ ፡ ትንታግ ፡ አይደለምን ፡ አለው ።

3 ፤ ኢያሱም ፡ እድፋም ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ በመልአኩ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ ነበር ። ርሱም ፡ መልሶ ፡ በፊቱ ፡
የቆሙትን ፦ እድፋሙን ፡ ልብስ ፡ ከርሱ ፡ ላይ ፡ አውልቁ ፡ አላቸው ። ርሱንም ፦ እንሆ ፥ አበሳኽን ፡ ከአንተ ፡
አርቄያለኹ ፥ ጥሩ ፡ ልብስም ፡ አለብስኻለኹ ፡ አለው ።

5 ፤ ደግሞ ፦ ንጹሕ ፡ ጥምጥም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አድርጉ ፡ አለ ። እነርሱም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ንጹሕ ፡ ጥምጥም ፡
አደረጉ ፥ ልብስንም ፡ አለበሱት ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በአጠገቡ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

6 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በኢያሱ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አዳኘበት ።

7 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በመንገዴ ፡ ብትኼድ ፡ ትእዛዜንም ፡ ብትጠብቅ ፥ በቤቴ ፡ ላይ ፡
ትፈርዳለኽ ፥ አደባባዮቼንም ፡ ትጠብቃለኽ ፥ በዚህም ፡ ከቆሙት ፡ ከነዚህ ፡ ጋራ ፡ መግባትን ፡ እሰጣለኹ ።

8 ፤ ታላቁ ፡ ካህን ፡ ኢያሱ ፡ ሆይ ፥ ስማ ፤ በፊትኽም ፡ የሚቀመጡት ፡ ባልንጀራዎችኽ ፡ ለምልክት ፡ የሚኾኑ ፡ ሰዎች ፡
ናቸውና ፥ ይስሙ ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ ባሪያዬን ፡ ቍጥቋጥ ፡ አወጣለኹ ።

9 ፤ በኢያሱ ፡ ፊት ፡ ያኖርኹት ፡ ድንጋይ ፥ እንሆ ፥ አለ ፤ በአንዱ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ ዐይኖች ፡
አሉ ፤ እንሆ ፥ ቅርጹን ፡ እቀርጻለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ የዚያችንም ፡ ምድር ፡ በደል ፡ ባንድ ፡
ቀን ፡ አስወግዳለኹ ።

10 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ እያንዳንዱ ፡ ከወይኑና ፡ ከበለሱ ፡ በታች ፡ ኾኖ ፡
ባልንጀራውን ፡ ይጠራል ።

______________ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። ______________

ምዕራፍ ፡ 4 ።

1 ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡ መልአክ ፡ ተመልሶ ፡ ከእንቅልፉ ፡ እንደሚነቃ ፡ ሰው ፡ አነቃኝ ።

2 ፤ ርሱም ፦ የምታየው ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ አለኝ ። እኔም ፦ እንሆ ፥ ኹለንተናው ፡ ወርቅ ፡ የኾነውን ፡ መቅረዝ ፡
አየኹ ፤ የዘይትም ፡ ማሰሮ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፥ ሰባትም ፡ መብራቶች ፡ ነበሩበት ፤ በራሱም ፡ ላይ ፡ ለነበሩት ፡
መብራቶች ፡ ሰባት ፡ ቧንቧዎች ፡ ነበሯቸው ።

3 ፤ ኹለት ፡ የወይራ ፡ ዛፎች ፥ አንዱ ፡ በማሰሮው ፡ በስተቀኝ ፡ አንዱም ፡ በስተግራው ፡ ኾነው ፥ በአጠገቡ ፡ ነበሩ ፡
አልኹ ።

4 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ ለነበረውም ፡ መልአክ ፡ መልሼ ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፡ አልኹት ።

5 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረውም ፡ መልአክ ፡ መልሶ ፦ እነዚህ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡
አታውቅምን ፡ አለኝ ። እኔም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ አላውቅም ፡ አልኹ ።

6 ፤ መልሶም ፦ ለዘሩባቤል ፡ የተባለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦ በመንፈሴ ፡ እንጂ ፡ በኀይልና ፡
በብርታት ፡ አይደለም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

7 ፤ ታላቅ ፡ ተራራ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ምንድር ፡ ነኽ ፡ በዘሩባቤል ፡ ፊት ፡ ደልዳላ ፡ ሜዳ ፡
ትኾናለኽ ፤ ሰዎችም ፦ ሞገስ ፥ ሞገስ ፡ ይኹንለት ፡ ብለው ፡ እየጮኹ ፡ ርሱ ፡ መደምደሚያውን ፡ ድንጋይ ፡ ያወጣል ፡
ብሎ ፡ ተናገረኝ ።

8 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

9 ፤ የዘሩባቤል ፡ እጆች ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ መሠረቱ ፥ የርሱም ፡ እጆች ፡ ይፈጽሙታል ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡
ወደ ፡ እናንተ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ ታውቃላችኹ ።

10 ፤ የጥቂቱን ፡ ነገር ፡ ቀን ፡ የናቀ ፡ ማን ፡ ነው ፡ እነዚህ ፡ ሰባቱ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ በዘሩባቤል ፡ እጅ ፡ ቱንቢውን ፡
ያያሉ ፤ እነዚህም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ የሚዘዋወሩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዐይኖች ፡ ናቸው ።

11 ፤ እኔም ፡ መልሼ ፦ በመቅረዙ ፡ በስተቀኝና ፡ በስተግራ ፡ ያሉ ፡ እነዚህ ፡ ኹለት ፡ የወይራ ፡ ዛፎች ፡ ምንድር ፡



www.ethiopianorthodox.org

ናቸው ፡ አልኹት ።

12 ፤ ኹለተኛም ፡ መልኼ ፦ በኹለቱ ፡ የወርቅ ፡ ቧንቧዎች ፡ አጠገብ ፡ ኾነው ፡ የወርቁን ፡ ዘይት ፡ የሚያፈሱ ፡ እነዚህ ፡ ኹለት ፡ የወይራ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፡ አልኹት ።

13 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ እነዚህ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ አታውቅምን ፡ አለኝ ። እኔም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ አላውቅም ፡ አልኹት ።

14 ፤ ርሱም ፦ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ጌታ ፡ አጠገብ ፡ የቆሙት ፡ ኹለቱ ፡ የተቀቡት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፡ አለኝ ።

## ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ምዕራፍ ፡ 5 ።

1 ፤ ተመልሼም ፡ ዐይኖቼን ፡ አነሣኹ ፥ እንሆም ፥ አንድ ፡ በራሪ ፡ የመጽሐፍ ፡ ጥቅል ፡ አየኹ ።

2 ፤ ርሱም ፦ የምታየው ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ አለኝ ። እኔም ፦ በራሪ ፡ የመጽሐፍ ፡ ጥቅል ፡ አያለኹ ፤ ርዝመቱ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ነው ፡ አልኹ ።

3 ፤ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ ይህ ፡ በምድር ፡ ፊት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የሚወጣው ፡ ርግማን ፡ ነው ፤ የሚሰርቅ ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ እንደተጻፈው ፡ ኹሉ ፡ ይጠፋል ፥ በሐሰት ፡ የሚምልም ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ እንደተጻፈው ፡ ኹሉ ፡ ይጠፋል ።

4 ፤ እኔ ፡ አስወጣዋለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ ወደሚሰርቀውም ፡ ቤት ፥ በሐሰትም ፡ በስሜ ፡ ወደሚምለው ፡ ቤት ፡ ይገባል ፤ በቤቱም ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል ፥ ርሱንም ፥ ዕንጨቱንና ፡ ድንጋዩን ፥ ይበላል ።

5 ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡ መልአክ ፡ ወጥቶ ፦ ዐይኖችኽን ፡ አንሣ ፥ ይህችም ፡ የምትወጣው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ እይ ፡ አለኝ ።

6 ፤ እኔም ፦ ምንድር ፡ ናት ፡ አልኹ ። ርሱም ፦ ይህች ፡ የምትወጣው ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ናት ፡ አለኝ ። ደግሞም ፦ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ በደላቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ።

7 ፤ እንሆም ፥ የርሳሱን ፡ መክሊት ፡ አነሡት ፤ እንሆም ፥ በኢፍ ፡ መስፈሪያው ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ተቀምጣ ፡ ነበር ።

8 ፤ ርሱም ፦ ይህች ፡ ክፋት ፡ ናት ፡ አለኝ ፤ በኢፍ ፡ መስፈሪያው ፡ ውስጥ ፡ ጣላት ፥ የርሳሱንም ፡ ጠገራ ፡ በመስፈሪያ ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ጣለ ።

9 ፤ ዐይኖቼንም ፡ አንሥቼ ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፥ ኹለት ፡ ሴቶች ፡ ወጡ ፥ ነፋስም ፡ በክንፎቻቸው ፡ ነበረ ፤ ክንፎቻቸውም ፡ እንደ ፡ ሽመላ ፡ ክንፎች ፡ ነበሩ ፤ የኢፍ ፡ መስፈሪያውንም ፡ በምድርና ፡ በሰማይ ፡ መካከል ፡ አነሡት ።

10 ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረውን ፡ መልአክ ፦ እነዚህ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያውን ፡ ወዴት ፡ ይወስዱታል ፡ አልኹት ።

11 ፤ ርሱም ፦ በሰናዖር ፡ ምድር ፡ ቤት ፡ ይሠሩለት ፡ ዘንድ ፡ ይወስዱታል ፤ በተዘጋጀም ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ በስፍራው ፡ ይኖራል ፡ አለኝ ።

## ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ምዕራፍ ፡ 6 ።

1 ፤ ተመልሼም ፡ ዐይኖቼን ፡ አነሣኹ ፥ እንሆም ፥ አራት ፡ ሠረገላዎች ፡ ከኹለት ፡ ተራራ ፡ መካከል ፡ ሲወጡ ፡ አየኹ ፤ ተራራዎቹም ፡ የናስ ፡ ተራራዎች ፡ ነበሩ ።

2 ፤ በፊተኛው ፡ ሠረገላ ፡ መጋላ ፡ ፈረሶች ፥ በኹለተኛውም ፡ ሠረገላ ፡ ዱሪ ፡ ፈረሶች ፡ ነበሩ ፥

3 ፤ በሦስተኛውም ፡ ሠረገላ ፡ ዐምባላይ ፡ ፈረሶች ፥ በአራተኛውም ፡ ሠረገላ ፡ ቅጥልጣል ፡ ፈረሶች ፡ ነበሩ ።

4 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ ለነበረውም ፡ መልአክ ፡ መልኼ ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፡ አልኹት ።



www.ethiopianorthodox.org

5 ፤ መልአኩም ፡ መልሶ ፦ እነዚህ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ከቆሙበት ፡ ስፍራ ፡ የሚወጡ ፡ አራቱ ፡ የሰማይ ፡ ነፋሳት ፡ ናቸው ።

6 ፤ ዱሪ ፡ ፈረሶች ፡ ያሉበት ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ይወጣል ፤ ዐምባላዮቹም ፡ ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ ይወጣሉ ፥ ቅጥልጣሎችም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይወጣሉ ፡ አለኝ ።

7 ፤ መጋላዎቹም ፡ ደግሞ ፡ ወጡ ፡ በምድርም ፡ ይመላለሱ ፡ ዘንድ ፡ ለመኼድ ፡ ይፈልጉ ፡
ነበር ፤ ርሱም ፦ ኺዱ ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ ተመላለሱ ፡ አለ ። እነርሱም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተመላለሱ ።

8 ፤ ጮኾም ፦ እንሆ ፥ ወደሰሜን ፡ ምድር ፡ የሚወጡት ፡ እነርሱ ፡ መንፈሴን ፡ በሰሜን ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ አሳርፈዋል ፡ ብሎ ፡ ተናገረኝ ።

9 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

10 ፤ ከባቢሎን ፡ ከመጡት ፡ ምርኮኛዎች ፡ ከሔልዳይና ፡ ከጦብያ ፡ ከዮዳዔም ፡ ውሰድ ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ መጥተኽ ፡ ወደሶፎንያስ ፡ ልጅ ፡ ወደኢዮስያስ ፡ ቤት ፡ ግባ ።

11 ፤ ብርንና ፡ ወርቅን ፡ ከነርሱ ፡ ውሰድ ፥ አክሊሎችንም ፡ ሥራ ፤ በታላቁም ፡ ካህን ፡ በኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ በኢያሱ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ድፋቸው ፥

12 ፤ እንዲህም ፡ በለው ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ስሙ ፡ ቍጥቋጥ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ በስፍራው ፡ ይበቅላል ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ መቅደስ ፡ ይሠራል ።

13 ፤ ርሱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መቅደስ ፡ ይሠራል ፥ ክብርንም ፡ ይሸከማል ፥ በዙፋኑም ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡
ይነግሣል ፤ በዙፋኑም ፡ ላይ ፡ ካህን ፡ ይኾናል ፥ የሰላምም ፡ ምክር ፡ በኹለቱ ፡ መካከል ፡ ይኾናል ።

14 ፤ አክሊሎችም ፡ ለሔሌምና ፡ ለጦብያ ፡ ለዮዳዔም ፡ ለሶፎንያስም ፡ ልጅ ፡ ለሔን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ለመታሰቢያ ፡ ይኾናሉ ።

15 ፤ በሩቅም ፡ ያሉት ፡ መጥተው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መቅደስ ፡ ይሠራሉ ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ ታውቃላችኹ ። የአምላካችኹንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አጥብቃችኹ ፡ ብትሰሙ ፡ ይህ ፡ ይኾናል ።

## ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ምዕራፍ ፡ 7 ።

1 ፤ በንጉሡም ፡ በዳርዮስ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ካሴሉ ፡ በሚባል ፡ በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ በአራተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ዘካርያስ ፡ መጣ ።

2 ፤ የቤቴልም ፡ ሰዎች ፡ ሳራሳርንና ፡ ሬጌሜሌክን ፡ ሰዎቻቸውንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይለምኑ ፡ ዘንድ ፥

3 ፤ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ካህናት ፡ ለነቢያትም ፦ ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ እንዳደረግኹት ፡
በዐምስተኛው ፡ ወር ፡ መለየትና ፡ ማልቀስ ፡ ይገባኛልን ፧ ብለው ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ ልኳቸው ፡ ነበር ።

4 ፤ የሰራዊትም ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

5 ፤ ለምድሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ለካህናትም ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ተናገራቸው ፦ በዚህ ፡ በሰባው ፡ ዓመት ፡ በዐምስተኛውና ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በጾማችኹና ፡ ባለቀሳችኹ ፡ ጊዜ ፥ በእውኑ ፡ ለእኔ ፡ ጾም ፡ ጾማችኹልኝ ፧

6 ፤ በምትበሉበትና ፡ በምትጠጡበትስ ፡ ጊዜ ፥ ለራሳችኹ ፡ የምትበሉና ፡ የምትጠጡ ፡ አይደላችኹምን ፧

7 ፤ ኢየሩሳሌምና ፡ በዙሪያዋ ፡ ያሉ ፡ ከተማዎች ፡ ገና ፡ ሰዎች ፡ ባሉባቸው ፡ ጊዜ ፥ በምቾትም ፡ ተቀምጠው ፡
ሳሉ ፥ ደቡቡና ፡ ቈላውም ፡ ሰዎች ፡ ባሉባቸው ፡ ጊዜ ፥ እግዚአብሔር ፡ በቀደሙት ፡ ነቢያት ፡ እጅ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ መስማት ፡ አይገባችኹምን ፧

8 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ዘካርያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦



www.ethiopianorthodox.org

9 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናግሯል ፦ እውነተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ፍረዱ ፤ ቸርነትንና ፡
ምሕረትን ፡ ሁላችኹ ፡ ለወንድሞቻችኹ ፡ አድርጉ ፤

10 ፤ መበለቲቱንና ፡ ድኻ ፡ አደጉን ፥ መጻተኛውንና ፡ ችግረኛውን ፡ አትበድሉ ፤ ከእናንተም ፡ ማንም ፡ በወንድሙ ፡
ላይ ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ በልቡ ፡ አያስብ ።

11 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ደንደሳቸውን ፡ አዞሩ ፡ እንጂ ፡ መስማትን ፡ እምቢ ፡ አሉ ፤ እንዳይሰሙም ፡ ጆሯቸውን ፡ አደነቈሩ ።

12 ፤ የሰራዊትም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቀደሙት ፡ ነቢያት ፡ እጅ ፡ በመንፈሱ ፡ የላከውን ፡ ሕጉንና ፡ ቃሉን ፡
እንዳይሰሙ ፡ ልባቸውን ፡ እንደ ፡ አልማዝ ፡ አጠነከሩ ፤ ስለዚህ ፥ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡
ቍጣ ፡ መጣ ።

13 ፤ እኔ ፡ በጠራኹ ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ እንዳልሰሙኝ ፥ እንዲሁ ፡ እነርሱ ፡ በሚጠሩበት ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ አልሰማም ፥ ይላል ፡
የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤

14 ፤ ወደማያውቋቸውም ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ በተንኋቸው ። እንዲሁ ፡ ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ ምድሪቱ ፡
ባድማ ፡ ኾናለች ፥ የሚተላለፍባትና ፡ የሚመላለስባትም ፡ አልነበረም ፤ ያማረችውንም ፡ ምድር ፡ ባድማ ፡ አደረጓት ።

________________ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ። ________________

ምዕራፍ ፡ 8 ።

1 ፤ የሰራዊትም ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

2 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለ ፡ ጽዮን ፡ ታላቅ ፡ ቅንአት ፡ ቀንቻለኹ ፥ በታላቅም ፡ ቍጣ ፡
ስለ ፡ ርሷ ፡ ቀንቻለኹ ።

3 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደ ፡ ጽዮን ፡ ተመልሻለኹ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ መካከል ፡
እኖራለኹ ፤ ኢየሩሳሌምም ፡ የእውነት ፡ ከተማ ፡ ትባላለች ፤ የሰራዊትም ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ የተቀደሰ ፡
ተራራ ፡ ይባላል ።

4 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ዳግመኛ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ባልቴቶች ፡ በኢየሩሳሌም ፡
አደባባይ ፡ ይቀመጣሉ ፤ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ከዕድሜው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ምርኵዝ ፡ በእጁ ፡ ይይዛል ።

5 ፤ የከተማዪቱም ፡ አደባባዮች ፡ በእነዚያ ፡ በሚጫወቱ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ይሞላሉ ።

6 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዚህ ፡ ወራት ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ቅሬታ ፡ ዐይን ፡ ዘንድ ፡ ድንቅ ፡
ቢኾን ፥ በእውኑ ፡ በእኔ ፡ ዐይን ፡ ዘንድ ፡ ደግሞ ፡ ድንቅ ፡ ይኾናልን ፧ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

7 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነሆ ፥ ሕዝቤን ፡ ከምሥራቅ ፡ ምድርና ፡ ከምዕራብ ፡ ምድር ፡
አድነዋለኹ ፤

8 ፤ አመጣቸዋለኹም ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ ፤ እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑኛል ፥ እኔም ፡ በእውነትና ፡
በጽድቅ ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ።

9 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ መቅደሱ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡
ቤት ፡ ከተመሠረተበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ከነቢያት ፡ አፍ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የሰማችኹ ፡ እናንተ ፡
ሆይ ፥ እጃችኹን ፡ አበርቱ ።

10 ፤ ከዚያ ፡ ወራት ፡ አስቀድሞ ፡ ለሰውና ፡ ለእንስሳ ፡ ዋጋ ፡ አልነበረምና ፤ እኔም ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ በወንድሙ ፡ ላይ ፡
አስነሥቼ ፡ ነበርና ፥ ካስጨናቂው ፡ የተነሣ ፡ ለሚገባውና ፡ ለሚወጣው ፡ ሰላም ፡ አልነበረም ።

11 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ቀደመው ፡ ዘመን ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ቅሬታ ፡ ላይ ፡ አልኾንም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡
እግዚአብሔር ።

12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሰላምን ፡ እዘራለኹ ፤ ወይኑ ፡ ፍሬውን ፡ ይሰጣል ፥ ምድርም ፡ አዝመራዋን ፡ ታወጣለች ፥ ሰማያትም ፡
ጠላቸውን ፡ ይሰጣሉ ፤ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ ቅሬታ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አወርሳለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

13 ፤ የይሁዳ ፡ ቤትና ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ርግማን ፡ እንደ ፡ ነበራችኹ ፥ እንዲሁ ፡
አድናችኋለኹ ፥ በረከትም ፡ ትኾናላችኹ ፤ አትፍሩ ፥ እጃችኹንም ፡ አበርቱ ።

14 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ አባቶቻችኹ ፡ እጅግ ፡ ባስቈጡኝ ፡ ጊዜ ፡ ክፉ ፡ ለማድረግ ፡
እንዳሰብኹ ፥ እንዳልተጸጸትኹም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥

15 ፤ እንዲሁ ፡ ዳግመኛ ፡ ለኢየሩሳሌምና ፡ ለይሁዳ ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ወራት ፡ በጎነትን ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡
ዐስቤያለኹ ፤ አትፍሩ ።

16 ፤ የምትሠሩት ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እያንዳንዳችኹ ፡ ከባልንጀራችኹ ፡ ጋራ ፡ እውነትን ፡ ተነጋገሩ ፤ በበር ፡
አደባባያችኹም ፡ የእውነትንና ፡ የሰላምን ፡ ፍርድ ፡ ፍረዱ ፤

17 ፤ ኹላችኹም ፡ በባልንጀራችኹ ፡ ላይ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ በልባችኹ ፡ አታስቡ ፤ የሐሰትንም ፡ መሐላ ፡
አትውደዱ ፤ ይህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እጠላለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

18 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

19 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የአራተኛው ፡ ወር ፡ ጾም ፡ የዐምስተኛውም ፡ የሰባተኛውም ፡
የዐሥረኛውም ፡ ወር ፡ ጾም ፡ ለይሁዳ ፡ ቤት ፡ ደስታና ፡ ተድላ ፡ የሐሤትም ፡ በዓላት ፡ ይኾናል ፤ ስለዚህም ፡ እውነትንና ፡
ሰላምን ፡ ውደዱ ።

20 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በብዙ ፡ ከተማዎች ፡ የሚቀመጡ ፡ አሕዛብ ፡ ገና ፡ ይመጣሉ ፤

21 ፤ በአንዲትም ፡ ከተማ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፦ እግዚአብሔርን ፡ እንለምን ፡ ዘንድ ፥ የሰራዊትንም ፡ ጌታ ፡
እግዚአብሔርን ፡ እንፈልግ ፡ ዘንድ ፡ ኑ ፡ እንኺድ ፤ እኔም ፡ እኼዳለኹ ፡ እያሉ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ከተማ ፡ ይኼዳሉ ።

22 ፤ ብዙ ፡ ወገኖችና ፡ ኀይለኛዎች ፡ አሕዛብ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሰራዊትን ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈልጉ ፡
ዘንድ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ይለምኑ ፡ ዘንድ ፡ ይመጣሉ ።

23 ፤ የሰራዊትም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ከአሕዛብ ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ ዐሥር ፡ ሰዎች ፡
የአንዱን ፡ አይሁዳዊ ፡ ሰው ፡ ልብስ ፡ ዘርፍ ፡ ይዘው ፦ እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እንዳለ ፡ ሰምተናልና ፥ ከእናንተ ፡
ጋራ ፡ እንኺድ ፡ ይላሉ ።

## ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ምዕራፍ ፡ 9 ።

1 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሸክም ፡ በሴድራክ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ነው ፥ በደማስቆም ፡ ላይ ፡ ያርፋል ፤ የእግዚአብሔር ፡
ዐይን ፡ ወደ ፡ ሰውና ፡ ወደእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤

2 ፤ ደግሞም ፡ በዳርቻዋ ፡ ባለችው ፡ በሐማት ፡ ላይ ፥ እጅግ ፡ ጠቢበኛዎች ፡ በኾኑ ፡ በጢሮስና ፡ በሲዶና ፡ ላይ ፡ ነው ።

3 ፤ ጢሮስም ፡ ምሽግን ፡ ለራሷ ፡ ሠርታለች ፥ ብሩንም ፡ እንደ ፡ ዐፈር ፥ ጥሩውንም ፡ ወርቅ ፡ እንደ ፡ መንገድ ፡ ጭቃ ፡
አከማችታለች ።

4 ፤ እንሆ ፥ ጌታ ፡ ይገፋታል ፥ በባሕርም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ብርታቷን ፡ ይመታል ፤ ርሷም ፡ በእሳት ፡ ትበላለች ።

5 ፤ አስቀሎና ፡ አይታ ፡ ትፈራለች ፤ ጋዛ ፡ ደግሞ ፡ አይታ ፡ እጅግ ፡ ትታመማለች ፤ ዐቃሮንም ፡ እንዲሁ ፥ ተስፋዋ ፡
ይቈረጣልና ፤ ንጉሡም ፡ ከጋዛ ፡ ይጠፋል ፥ በአስቀሎናም ፡ የሚቀመጥ ፡ አይገኝም ።

6 ፤ የተደባለቀ ፡ ወገን ፡ በአዛጦን ፡ ይቀመጣል ፥ የፍልስጥኤማውያንንም ፡ ትዕቢት ፡ አጠፋለኹ ።

7 ፤ ደሙንም ፡ ከአፉ ፡ ውስጥ ፡ ርኩሱንም ፡ ነገር ፡ ከጥርሱ ፡ መካከል ፡ አስወግዳለኹ ፤ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ ለአምላካችን ፡
ቅሬታ ፡ ይኾናል ፤ በይሁዳም ፡ እንደ ፡ አለቃ ፡ ይኾናል ፥ ዐቃሮንም ፡ እንደ ፡ ኢያቡሳዊ ፡ ይኾናል ።

8 ፤ እኔም ፡ ማንም ፡ እንዳይኼድና ፡ እንዳይመለስ ፡ እንደ ፡ ጠባቂ ፡ ጦር ፡ ኾኖ ፡ በቤቴ ፡ ዙሪያ ፡ ሰፈር ፡
አደርጋለኹ ፤ አኹንም ፡ በዐይኔ ፡ አይቻለኹና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አስጨናቂ ፡ አያልፍባቸውም ።



www.ethiopianorthodox.org

9 ፤ አንቺ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይበልሽ ፤ አንቺ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እልል ፡
በዪ ፤ እንሆ ፥ ንጉሥሽ ፡ ጻድቅና ፡ አዳኝ ፡ ነው ፤ ትሑትም ፡ ኾኖ ፡ በአህያም ፥ በአህያዪቱ ፡ ግልገል ፡ በውርንጫዪቱ ፡
ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣል ።

10 ፤ ሠረገላውንም ፡ ከኤፍሬም ፡ ፈረሱንም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ አጠፋለኹ ፤ የሰልፉም ፡ ቀስት ፡ ይሰበራል ፥ ለአሕዛብም ፡
ሰላምን ፡ ይናገራል ፤ ግዛቱም ፡ ከባሕር ፡ እስከ ፡ ባሕር ፥ ከወንዙም ፡ እስከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድርስ ፡ ይኾናል ።

11 ፤ ላንቺም ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ቃል ፡ኪዳንሽ ፡ ደም ፥ እስሮችሽን ፡ ውሃ ፡ ከሌለበት ፡ ጕድጓድ ፡ አውጥቻለኹ ።

12 ፤ እናንተ ፡ በተስፋ ፡ የምትኖሩ ፡ እስሮች ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ጽኑ ፡ ዐምባ ፡ ተመለሱ ፤ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ አድርጌ ፡
እንድመልስልሽ ፡ ዛሬ ፡ እነግርሻለኹ ።

13 ፤ ይሁዳን ፡ ለእኔ ፡ ገትሬያለኹ ፤ ቀስቱን ፡ በኤፍሬም ፡ ሞልቻለኹ ፤ ጽዮን ፡ ሆይ ፥ ልጆችሽን ፡ በግሪክ ፡ ልጆች ፡
ላይ ፡ አስነሣለኹ ፥ አንቺንም ፡ እንደ ፡ ኀያል ፡ ሰው ፡ ሰይፍ ፡ አደርግሻለኹ ።

14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ይገለጣል ፥ ፍላጻውም ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ይወጣል ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡
መለከትን ፡ ይነፋል ፥ በደቡብም ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይኼዳል ።

15 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጠብቃቸዋል ፤ እነርሱም ፡ ይበሏቸዋል ፥ የወንጭፉንም ፡ ድንጋዮች ፡
ይረግጣሉ ፤ እንደ ፡ ወይን ፡ ጠጅም ፡ ይጠጧቸዋል ፥ እንደ ፡ ጥዋዎችም ፡ እንደ ፡ መሠዊያም ፡ ማእዘኖች ፡ የተሞሉ ፡
ይኾናሉ ።

16 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሕዝቡ ፡ መንጋ ፡ ያድናቸዋል ፤ እነርሱም ፡ ለአክሊል ፡
እንደሚኾኑ ፡ እንደ ፡ ከበሩ ፡ ድንጋዮች ፡ ይኾናሉ ፥ በምድሩም ፡ ላይ ፡ ይብለጨለጫሉ ።

17 ፤ በጎነቱ ፡ እንዴት ፡ ታላቅ ፡ ነው! ውበቱስ ፡ እንዴት ፡ ታላቅ ፡ ነው! እኽል ፡ ጕበዛዝቱን ፥ ጕሽ ፡ ጠጅም ፡
ቈነገዣጕቱን ፡ ያለመልማል ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ምዕራፍ ፡ 10 ።

1 ፤ በኋለኛው ፡ ዝናብ ፡ ጊዜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዝናቡን ፡ ለምኑ ፤ እግዚአብሔር ፡ መብረቅ ፡
ያደርጋል ፤ ርሱም ፡ የበልግ ፡ ዝናብን ፡ ለያንዳንዱም ፡ በሜዳ ፡ ውስጥ ፡ ሣርን ፡ ይሰጣል ።

2 ፤ ተራፊም ፡ ከንቱነትን ፡ ተናግረዋልና ፥ ሟርተኛዎችም ፡ ውሸትን ፡ አይተዋልና ፤ ሕልምንም ፡ የሚያዩ ፡ በሐሰት ፡
ተናግረዋል ፥ በከንቱም ፡ ያጽናናሉ ፤ እረኛም ፡ የላቸውምና ፡ እንደ ፡ በጎች ፡ ተቅበዝብዘዋል ፡ ተጨንቀውማል ።

3 ፤ ቍጣዬ ፡ በእረኛዎች ፡ ላይ ፡ ነዷል ፥ አውራ ፡ ፍየሎችንም ፡ እቀጣለኹ ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡
የይሁዳን ፡ ቤት ፡ መንጋውን ፡ ጐብኝቷል ፥ በሰልፍም ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ ክብሩ ፡ ፈረስ ፡ ያደርጋቸዋል ።

4 ፤ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ የማእዘኑ ፡ ድንጋይ ፥ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ ችንካሩ ፥ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ የሰልፉ ፡ ቀስት ፥ ከርሱም ፡
ዘንድ ፡ አስገባሪው ፡ ዅሉ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ይመጣሉ ።

5 ፤ በሰልፍም ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ በመንገድ ፡ ጭቃ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚረግጡ ፡ ኀያላን ፡ ይኾናሉ ፤ እግዚአብሔርም ፡
ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ ይዋጋሉ ፥ ፈረሰኛዎችም ፡ ያፍራሉ ።

6 ፤ ወድጃቸዋለኹና ፡ የይሁዳን ፡ ቤት ፡ አበረታለኹ ፥ የዮሴፍንም ፡ ቤት ፡
አድናለኹ ፤ አደላድላቸዋለኹም ፤ እመልሳቸዋለኹ ፤ እኔም ፡ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝና ፥ እኔም ፡
እሰማቸዋለኹና ፡ እንዳልጣልኋቸው ፡ ይኾናሉ ።

7 ፤ የኤፍሬምም ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ኀያላን ፡ ይኾናሉ ፥ ልባቸውም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንደ ፡ ጠጣ ፡ ሰው ፡ ደስ ፡
ይለዋል ፤ ልጆቻቸውም ፡ አይተው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፥ ልባቸውም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሐሤት ፡ ያደርጋል ።

8 ፤ ተቤዥቻቸዋለኹና ፡ በፉጨት ፡ ጠርቼ ፡ እሰበስባቸዋለኹ ፤ ቀድሞም ፡ በዝተው ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ይበዛሉ ።

9 ፤ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ብዘራቸው ፡ እንኳ ፡ በሩቅ ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ ያስቡኛል ፥ ከልጆቻቸውም ፡ ጋራ ፡ በሕይወት ፡


www.ethiopianorthodox.org

ይኖራሉ ፥ ይመለሱማል ።

10 ፤ ከግብጽም ፡ ምድር ፡ እመልሳቸዋለኹ ፥ ከአሶርም ፡ እሰበስባቸዋለኹ ፤ ወደ ፡ ገለዓድና ፡ ወደሊባኖስ ፡ ምድር ፡
አመጣቸዋለኹ ፥ የሚበቃም ፡ ቦታ ፡ አይገኝላቸውም ።

11 ፤ ርሱም ፡ በጭንቅ ፡ ባሕር ፡ ያልፋል ፥ የባሕርንም ፡ ሞገድ ፡ ይመታል ፥ የወንዙም ፡ ጥልቅ ፡ ዅሉ ፡
ይደርቃል ፤ የአሶርም ፡ ትዕቢት ፡ ይዋረዳል ፥ የግብጽም ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ ይርቃል ።

12 ፤ በአምላካቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ አበረታቸዋለኹ ፥ በስሙም ፡ ይመካሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ምዕራፍ ፡ 11 ።

1 ፤ ሊባኖስ ፡ ሆይ ፥ ደጆችኽን ፡ ክፈት ፥ እሳትም ፡ ዝግባዎችኽን ፡ ትብላ ።

2 ፤ የጥድ ፡ ዛፍ ፡ ሆይ ፥ ዝግባ ፡ ወድቋልና ፥ ከበርቴዎችም ፡ ጠፍተዋልና ፥ ዋይ ፡ በል ፤ እናንተም ፡ የባሳን ፡ ዛፎች ፡
ሆይ ፥ ጽኑው ፡ ጫካ ፡ ተቈርጧልና ፥ ዋይ ፡ በሉ ።

3 ፤ የእረኞዎች ፡ ክብር ፡ ተዋርዷልና ፥ የዋይታቸው ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቷል ፤ የዮርዳኖስ ፡ ትዕቢት ፡
ተዋርዷልና ፥ የአንበሳዎች ፡ ግሣት ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቷል ።

4 ፤ አምላኬ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ፦ ለዕርድ ፡ የሚኾኑትን ፡ በጎች ፡ ጠብቅ ።

5 ፤ የገዟቸው ፡ ያርዷቸዋል ፥ ራሳቸውንም ፡ እንደ ፡ በደለኞዎች ፡ አድርገው ፡ አይቈጥሩም ፤ የሸጧቸውም ፦ ባለጠጋ ፡
ኾነናልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ይላሉ ፤ እረኞዎቻቸውም ፡ አይራሩላቸውም ።

6 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ለሚኖሩ ፡ አልራራም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እንሆም ፥ ሰውን ፡ ዅሉ ፡
በባልንጀራውና ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፤ ምድሪቱንም ፡ ይመታሉ ፥ ከእጃቸውም ፡ አላድናቸውም ።

7 ፤ እኔም ፡ ለዕርድ ፡ የሚኾኑትን ፡ በጎች ፥ የመንጋውን ፡ ችግረኞዎች ፡ ጠበቅኹ ። ኹለት ፡ በትሮችንም ፡
ወሰድኹ ፤ የአንዲቱን ፡ ስም ፡ ውበት ፡ የኹለተኛዪቱንም ፡ ስም ፡ ማሰሪያ ፡ ብዬ ፡ ጠራኹ ፤ መንጋውንም ፡ ጠበቅኹ ።

8 ፤ ባንድ ፡ ወርም ፡ ሦስቱን ፡ እረኞዎች ፡ አጠፋኹ ፤ ነፍሴም ፡ ተሰቀቀቻቸው ፥ ነፍሳቸውም ፡ ደግሞ ፡ እኔን ፡ ጠላች ።

9 ፤ እኔም ፦ እናንተን ፡ አልጠብቅም ፤ የሚሞተው ፡ ይሙት ፥ የሚጠፋውም ፡ ይጥፋ ፤ የቀረውም ፡ እያንዳንዱ ፡
የባልንጀራውን ፡ ሥጋ ፡ ይብላ ፡ አልኹ ።

10 ፤ እኔም ፡ ከሕዝቦች ፡ ዅሉ ፡ ጋራ ፡ የገባኹትን ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ አፈርስ ፡ ዘንድ ፡ ውበት ፡ የተባለችውን ፡ በትሬን ፡
ወስጄ ፡ ቈረጥኹ ።

11 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ተሰበረች ፤ እንዲሁም ፡ እኔን ፡ የተመለከቱ ፡ የመንጋው ፡ ችግረኞዎች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
እንደ ፡ ነበረ ፡ ዐወቁ ።

12 ፤ እኔም ፦ ደስ ፡ ብሏችኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዋጋዬን ፡ስጡኝ ፤ ያለዚያ ፡ ግን ፡ ተዉት ፡ አልኹ ። እነርሱም ፡ ለዋጋዬ ፡
ሠላሳ ፡ ብር ፡ መዘኑ ።

13 ፤ እግዚአብሔርም ፦ የተስማሙበትን ፡ የከበረውን ፡ ዋጋዬን ፡ በግምጃ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አኑረው ፡ አለኝ ። እኔም ፡
ሠላሳውን ፡ ብር ፡ ወስጄ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ባለው ፡ በግምጃ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አኖርኹት ።

14 ፤ በይሁዳና ፡ በእስራኤል ፡ መካከል ፡ ያለውንም ፡ ወንድማማችነት ፡ እሰብር ፡ ዘንድ ፡ ማሰሪያ ፡ የተባለችውን ፡
ኹለተኛዪቱን ፡ በትሬን ፡ ቈረጥኹ ።

15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ዳግመኛም ፡ የሰነፍን ፡ እረኛ ፡ ዕቃ ፡ ውሰድ ።

16 ፤ እንሆ ፥ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ እረኛ ፡ አስነሣለኹ ፤ ርሱም ፡ የጠፋውን ፡ አያስብም ፥ የባዘነውን ፡
አይፈልግም ፥ የተሰበረውን ፡ አይጠግንም ፤ የዳነውንም ፡ አይቀልብም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የሰባውን ፡ ሥጋ ፡
ይበላል ፥ ሰኰናውንም ፡ ይቀለጣጥማል ።



www.ethiopianorthodox.org

17 ፤ መንጋውን ፡ ለሚተው ፡ ለምናምንቴ ፡ እረኛ ፡ ወዮለት! ሰይፍ ፡ በክንዱና ፡ በቀኝ ፡ ዐይኑ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ ክንዱም ፡ አጥብቃ ፡ ትደርቃለች ፥ ቀኝ ፡ ዐይኑም ፡ ፈጽሞ ፡ ትጨልማለች ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ምዕራፍ ፡ 12 ።

1 ፤ ስለ ፡ እስራኤል ፡ የተነገረ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሸክም ፡ ይህ ፡ ነው ፦ ሰማያትን ፡ የዘረጋ ፥ ምድርንም ፡ የመሠረተ ፥ የሰውንም ፡ መንፈስ ፡ በውስጡ ፡ የሠራ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

2 ፤ እንሆ ፥ ኢየሩሳሌምን ፡ በዙሪያዋ ፡ ላሉት ፡ ለአሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ የመንገድገድ ፡ ዋንጫ ፡ አደርጋታለኹ ፤ ደግሞም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ስትከበብ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ።

3 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ለአሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ከባድ ፡ ድንጋይ ፡ አደርጋታለኹ ፤ የሚሸከሟት ፡ ዅሉ ፡ እጅግ ፡ ይቈስላሉ ፤ የምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ በላይዋ ፡ ላይ ፡ ይከማቻሉ ።

4 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ፈረስን ፡ ዅሉ ፡ በድንጋጤ ፥ ተቀማጭንም ፡ በእብድነት ፡ እመታለኹ ፤ ዐይኖቼንም ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ እከፍታለኹ ፥ የአሕዛብንም ፡ ፈረሶች ፡ ዅሉ ፡ በዕውርነት ፡ እመታለኹ ።

5 ፤ የይሁዳም ፡ አለቃዎች ፡ በልባቸው ፦ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚኖሩ ፡ በአምላካቸው ፡ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ብርታት ፡ አለ ፡ ይላሉ ።

6 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ የይሁዳን ፡ አለቃዎች ፡ በዕንጨት ፡ መካከል ፡ እንዳለ ፡ ትንታግ ፥ በነዶዎችም ፡ መካከል ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ ፋና ፡ ነበልባል ፡ አደርጋቸዋለኹ ፤ በቀኝና ፡ በግራ ፡ በዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ይበላሉ ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በስፍራዋ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ትኖራለች ።

7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የዳዊት ፡ ቤት ፡ ክብርና ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፡ ክብር ፡ በይሁዳ ፡ ክብር ፡ ላይ ፡ እንዳይታበይ ፡ የይሁዳን ፡ ድንኳኖች ፡ አስቀድሞ ፡ ያድናል ።

8 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚኖሩት ፡ ይመክትላቸዋል ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከነርሱ ፡ መካከል ፡ ደካማው ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ይኾናል ፤ የዳዊትም ፡ ቤት ፡ በፊታቸው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ ይኾናል ።

9 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ የሚመጡትን ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ለማጥፋት ፡ እጋደላለኹ ።

10 ፤ በዳዊትም ፡ ቤት ፡ ላይ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፥ የሞገስንና ፡ የልመናን ፡ መንፈስ ፡ አፈሳለኹ ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ ወደወጉት ፡ ይመለከታሉ ፤ ሰውም ፡ ለአንድያ ፡ ልጁ ፡ እንደሚያለቅስ ፡ ያለቅሱለታል ፥ ሰውም ፡ ለበኵር ፡ ልጁ ፡ እንደሚያዝን ፡ በመራራ ፡ ሐዘን ፡ ያዝኑለታል ።

11 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ በመጊዶን ፡ ሜዳ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ እንደ ፡ ሐዳድሪሞን ፡ ልቅሶ ፡ ታላቅ ፡ ልቅሶ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይኾናል ።

12 ፤ ምድሪቱም ፡ ታለቅሳለች ፤ እያንዳንዱ ፡ ወገን ፡ ለብቻው ፥ የዳዊት ፡ ቤት ፡ ወገን ፡ ለብቻው ፥ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፤ የናታን ፡ ቤት ፡ ወገን ፡ ለብቻው ፥ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፤

13 ፤ የሌዊ ፡ ቤት ፡ ወገን ፡ ለብቻው ፥ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፤ የሰሜኢ ፡ ወገን ፡ ለብቻው ፥ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፤

14 ፤ የቀሩት ፡ ወገኖች ፡ ዅሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወገን ፡ ለብቻው ፥ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፡ ያለቅሳሉ ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ምዕራፍ ፡ 13 ።

1 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ለዳዊት ፡ ቤትና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚኖሩ ፡ ከኀጢአትና ፡ ከርኵሰት ፡ የሚያነጻ ፡ ምንጭ ፡ ይከፈታል ።

2 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ የጣዖታትን ፡ ስም ፡ ከምድር ፡ አጠፋለኹ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አይታሰቡም ፤ ደግሞም ፡ ሐሰተኛዎችን ፡ ነቢያትና ፡ ርኩስ ፡ መንፈስን ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ አስወግዳለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

3 ፤ ማንም ፡ ደግሞ ፡ ትንቢት ፡ ቢናገር ፡ የወለዱት ፡ አባቱና ፡ እናቱ ፦ አንተ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ሐሰትን ፡ ተናግረኻልና ፥ በሕይወት ፡ አትኖርም ፡ ይሉታል ፤ ትንቢትንም ፡ ሲናገር ፡ የወለዱት ፡ አባቱና ፡ እናቱ ፡ ይወጉታል ።

4 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ነቢያቱ ፡ ኹሉ ፡ ትንቢትን ፡ ሲናገሩ ፡ እያንዳንዱ ፡ ስለ ፡ ራእዩ ፡ ያፍራል ፤ ያታልሉም ፡ ዘንድ ፡ የማቅ ፡ ልብስ ፡ አይለብሱም ።

5 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ ከታናሽነቴ ፡ ዠምሮ ፡ ባሪያ ፡ ኾኜ ፡ ነበርኹና ፡ ገበሬ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ ነቢይ ፡ አይደለኹም ፡ ይላል ።

6 ፤ ሰውም ፦ ይህ ፡ በእጆችኽ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ቍስል ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ይለዋል ። ርሱም ፦ በወዳጆቼ ፡ ቤት ፡ የቈሰልኹት ፡ ቍስል ፡ ነው ፡ ይላል ።

7 ፤ ሰይፍ ፡ ሆይ ፥ ባልንጀራዬ ፡ በኾነው ፡ ሰው ፡ በእረኛዬ ፡ ላይ ፡ ንቃ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ እረኛውን ፡ ምታ ፥ በጎቹም ፡ ይበተናሉ ፤ እጄንም ፡ በታናናሾች ፡ ላይ ፡ እመልሳለኹ ።

8 ፤ በምድርም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ኹለት ፡ ክፍል ፡ ተቈርጠው ፡ ይሞታሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ሦስተኛውም ፡ ክፍል ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ይቀራል ።

9 ፤ ሦስተኛውንም ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ አገባለኹ ፥ ብርም ፡ እንደሚነጥር ፡ አነጥራቸዋለኹ ፥ ወርቅም ፡ እንደሚፈተን ፡ እፈትናቸዋለኹ ፤ እነርሱም ፡ ስሜን ፡ ይጠራሉ ፥ እኔም ፡ እሰማቸዋለኹ ፤ እኔም ፦ ይህ ፡ ሕዝቤ ፡ ነው ፡ እላለኹ ፤ ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ አምላኬ ፡ ነው ፡ ይላል ።

## ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ምዕራፍ ፡ 14 ።

1 ፤ እነሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ይመጣል ፥ ብዝበዛሽንም ፡ በውስጥሽ ፡ ይካፈላሉ ።

2 ፤ አሕዛብንም ፡ ኹሉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ለሰልፍ ፡ እሰበስባለኹ ፤ ከተማዪቱም ፡ ትያዛለች ፥ ቤቶችም ፡ ይበዘበዛሉ ፥ ሴቶችም ፡ ይነወራሉ ፤ የከተማዪቱም ፡ እኩሌታ ፡ ለምርኮ ፡ ይወጣል ፥ የቀረው ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ ከከተማ ፡ አይጠፋም ።

3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይወጣል ፥ በሰልፍም ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተዋጋ ፡ ከነዚያ ፡ አሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ይዋጋል ።

4 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግሮቹ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ትይዩ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ ላይ ፡ ይቆማሉ ፤ ደብረ ፡ ዘይትም ፡ በመካከል ፡ ወደ ፡ ምሥራቅና ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ይሰነጠቃል ፥ እጅግም ፡ ታላቅ ፡ ሸለቆ ፡ ይኾናል ፤ የተራራውም ፡ እኩሌታ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፥ እኩሌታውም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይርቃል ።

5 ፤ የተራራዎችም ፡ ሸለቆ ፡ እስከ ፡ አጸል ፡ ይደርሳልና ፥ በተራራዎች ፡ ሸለቆ ፡ ትሸሻላችኹ ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በዖዝያን ፡ ዘመን ፡ ከኾነው ፡ ከምድር ፡ መናወጥ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ሸሻችኹ ፡ ትሸሻላችኹ ፤ አምላኬ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከቅዱሳኑ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ይመጣል ።

6 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በረዶና ፡ ውርጭ ፡ እንጂ ፡ ብርሃን ፡ አይኾንም ።

7 ፤ አንድ ፡ ቀንም ፡ ይኾናል ፥ ርሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ይኾናል ፤ ቀንም ፡ አይኾንም ፥ ሌሊትም ፡ አይኾንም ፤ ሲመሽም ፡ ብርሃን ፡ ይኾናል ።

8 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የሕይወት ፡ ውሃ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ይወጣል ፤ እኩሌታው ፡ ወደምሥራቁ ፡ ባሕር ፥ እኩሌታውም ፡ ወደምዕራቡ ፡ ባሕር ፡ ይኼዳል ፤ ይህ ፡ በበጋና ፡ በክረምት ፡ ይኾናል ።

9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይነግሣል ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፥ ስሙም ፡ አንድ ፡ ይኾናል ።

10 ፤ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ከጌባ ፡ ዠምሮ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ እስካለችው ፡ እስከ ፡ ሬሞን ፡ ድረስ ፡ ተለውጣ ፡ እንደ ፡ ዐረባ ፡ ትኾናለች ፤ ርሷም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ትላለች ፥ ከብንያምም ፡ በር ፡ ዠምሮ ፡ እስከፊተኛው ፡ በር ፡ ስፍራ ፡ እስከማእዘኑ ፡ በር ፡ ድረስ ፥ ከሐናንኤልም ፡ ግንብ ፡ ዠምሮ ፡ እስከንጉሡ ፡ መጥመቂያ ፡ ድረስ ፡ በስፍራዋ ፡ ትኖራለች ።

http://www.gzamargna.net

www.ethiopianorthodox.org

11 ፤ ሰዎችም ፡ ይኖሩባታል ፥ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ርግማን ፡ አይኾንም ፤ ኢየሩሳሌምም ፡ ተዘልላ ፡ ትኖራለች ።

12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ጋራ ፡ የተዋጉትን ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ የሚቀሥፍበት ፡ ቸነፈር ፡ ይህ ፡
ነው ፤ በእግራቸው ፡ ሲቆሙ ፡ ሥጋቸው ፡ ይበሰብሳል ፥ ዐይኖቻቸውም ፡ በዐይኑ ፡ ሥባቸው ፡ ውስጥ ፡
ይበሰብሳሉ ፥ ምላሳቸውም ፡ በአፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ይበሰብሳል ።

13 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ሽብር ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ እያንዳንዱም ፡ የባልንጀራውን ፡
እጅ ፡ ይይዛል ፥ እጁም ፡ በባልንጀራው ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ይነሣል ።

14 ፤ ይሁዳም ፡ ደግሞ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ይዋጋል ፤ በዙሪያም ፡ ያሉት ፡ የአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ሀብት ፡ እጅግ ፡
ብዙ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ልብስም ፡ ይሰበሰባል ።

15 ፤ በፈረስና ፡ በበቅሎ ፥ በግመልና ፡ በአህያ ፥ በዚያም ፡ ሰፈር ፡ ባለ ፡ እንስሳ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የኾነ ፡ ቸነፈር ፡ እንደዚያ ፡
ያለ ፡ ቸነፈር ፡ ይኾናል ።

16 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ከመጡት ፡ ከአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ የቀሩት ፡ ኹሉ ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ይሰግዱ ፡ ዘንድ ፥ የዳስ ፡ በዓልንም ፡ ያከብሩ ፡ ዘንድ ፡ በየዓመቱ ፡ ይወጣሉ ።

17 ፤ ከምድርም ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሰግዱ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
ለማይወጡ ፡ ለእነርሱ ፡ ዝናብ ፡ አይዘንብላቸውም ።

18 ፤ የግብጽም ፡ ወገን ፡ ባይወጣ ፡ ወደዚያም ፡ ባይመጣ ፥ እግዚአብሔር ፡ የዳስ ፡ በዓልን ፡ ያከብሩ ፡ ዘንድ ፡
የማይወጡትን ፡ አሕዛብ ፡ የሚቀሥፍበት ፡ ቸነፈር ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

19 ፤ የግብጽ ፡ ቅጣት ፥ የዳስ ፡ በዓልንም ፡ ያከብሩ ፡ ዘንድ ፡ የማይወጡት ፡ የአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ቅጣት ፡ እንደዚህ ፡
ይኾናል ።

20 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ በፈረሶች ፡ ሻኵራ ፡ ላይ ፦ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ተብሎ ፡ ይጻፋል ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡
ያሉ ፡ ምንቸቶች ፡ በመሠዊያው ፡ ፊት ፡ እንዳሉ ፡ ዳካዎች ፡ ይኾናሉ ።

21 ፤ በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ ያሉ ፡ ምንቸቶችም ፡ ኹሉ ፡ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሱ ፡
ይኾናሉ ፤ የሚሠዉትም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ይመጣሉ ፡ ከነዚያም ፡ ወስደው ፡ ይቀቅሉባቸዋል ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በሰራዊት ፡
ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ከነዓናዊው ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ አይገኝም ፨



www.ethiopianorthodox.org